# ኢትዮጵያውያኖችና አሜሪካኖች ለፍትህና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ፤ ሎስ አንጀለስ

## በስሜን አሜሪካ  የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ስፖርተኞች
## በደም የተነከረ ገንዝብ አይገዛንም አሉ!!!!!

ታህሳስ 30፤ 2004

የኢትዮጵያን የእግር ኳስ ፌደሬሽን በሰሜን አሜሪካ ከተመሠረተ እነሆ 28 ዓመቱን በሚመጣው ጁላይ መጀመሪያ፣ 2012 ዓም በዳላስ በሚያከብረው ዓመታዊ በዓሉ በደማቅ ሁኔታ ለማስታወስ በዝግጅት ላይ ነው። ይህ ፌደሬሽን ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በስደት ለምንገኘው ኢትዮጵያውያን በዓመት አንዴ በአንድ ከተማ ከያለንበት በመምጣት ተሰባስበን እግር ኳሱን ብቻ ሳይሆን፤ ባህላችንን ለልጆቻችንና ለምንኖርበት ዓለም የምናስታዋውቅበት ወቅት ነው። የዚህን ዓመታዊና ኢትዮጵያዊ ባህል በተለይም ለወጣቱ ትውልድ የኢትዮጵያዊነት መሠረቱን የሚያስታውሰውና ከውድ ወገኖቹ ጋር በይበልጥ የሚያቀራርበው ለመሆኑም የሚያጠያይቅ አይደለም።

ይሁን እንጅ ዘረኛው የወያኔ መንግሥት በትረ ሥልጣን በሀይል ከተቆጣጠረ ጊዜ ጀምሮ ከተባባሪዎቹ ጋር በመሆን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የማያደርገውና የማይፈጽመው ተግባር እንደሌለ በሀያ ዓመታት አገዛዝ ዘመኑ በማያሻማ ሁኔታ አረጋግጠልናል። ይህ ኢትዮጵያዊነትንና ኢትዮጵያን በማፈራረስ ላይ ያለው የወያኔ ዘረኛ መንግስት በሆዳቸው ገዝቶ በሰሜን አሜሪካ የስፖርት ፌደሬሺን ውስጥ በመደባቸው ካድሬዎች የተሸረበውን የመበተን ሴራ በማክሸፍ *ገንዝብ ከአገርና ከታሪክ አይበልጥም ያሉ ቆራጥ ኢትዮጵያዊን ስፖርተኞች ፤ "በደም የተጨማለቀ ገንዝብ አንቀበልም!" ብለው መመለሳቸው ለሐቀኛ ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ ኩራት ሆኖአል። በጣም የሚገርመው እነዚህ ሀሊናቸውን የሸጡ ጥቂት ግለሰቦች ሀገር ወዳድ አባላቱን ለመደለል እነሱን ለተቀላቀለ ቡድን ለእያንዳንዱ በርካታ ገንዘብ እንደሚለግሱና የአውሮፕላንና የሆቴል ወጭዎችንም እንደሚሸፍኑ አስታውቀዋል። ይህን ያህል የገንዘብ ወጭ ከየት እንዳመጡት ሀሊና ላለው ወገን ሁሉ ለመገመት አያዳግተውም። ከዚህ ቀደምም በተመሳሳይ ሁኔታ ዘረኛው የወያኔ መንግሥት በጋሻ ጃግሬዎቹ በኩል ለዚሁ ተግባር የሚውል በርካታ ገንዘብ ሲያድል እንደነበረ የታወቀ ነው።*

ዛሬ በየምንኖርበት አካባቢዎች ሁሉ በሀይማኖት ተቋሞች፤ በንግድ ድርጅቶችና ማህበሮች፤ ኢትዮጵያውያኖች በሚሰባሰቡበት አካባቢ  ሁሉ ወያኔ የሰለላና የብተና ካድሬዎቹን በማሰማራት ቢቻል የወያኔ ተቀጥላ ድርጅት ማቋቋም ካልሆነም እንዲበተንና አባላቱ እንዲበጣበጡ እያደረጉ ነው። በቤተ ዕምነት ቦታዎች ሁሉ ስለሀገር መቆርቆር፤ የሕዝባችንን ብሶት ማሳወቅና ማውራት ሁሉ የፓለቲካ ጉዳይ ስለሆነ አይቻልም በሚሉ ጥቂት የወያኔ ተላላኪዎች አማካኝነት የሀገር ወዳዱን ጎራ ለማኮላሸት እየጣሩ ለመሆኑ የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን የሆንን ሁሉ በሚገባ የምናውቀው ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ሀገር ወዳድ ወገኖች ሁሉ አንድነታችንና ህብረታችንን በያለንበት አካባቢ ሁሉ ከነዚህ ከፋፋይና ፀረ ኢትዮጵያ ግለሰቦች ሴራ ተጠንቅቀን መጠበቅ ይኖርብናል።

የሰሜን አሜሪካ ስፖርት ፌደሬሽንን ነቅተው በመጠበቅ፤ ክነዚህ ከሀዲዎች ተከላክለው ያቆዩንና አሁንም ተንኮለኞቹ የፈለፈሉትን ሴራ ያከሸፉትን ወገኖች ከልብ ልናመሰግናቸው ይገባናል፤ ህዝብም በጎ ድርጊታችውን እንዲያውቅ የማድረግ ሁላችንም ሀላፊነት አለብን። በዚህ አኳያ በሎስ አንጀለስ የሚገኙት የዳሎል፤ የኤል ኤ ስታርስና የአበበ ቢቂላ የእግር ኳስ ማህበሮች እነኝህን ሆድ አደሮች አሳፍረው በመመለሳቸው መመስገንና አይዞአችሁ ሊባሉ ይገባል። እኛም በሎስ አንጀለስ የዲሞክራሲና ፍትህ በኢትዮጵያ ማህበር አባላት እነዚህን ሴረኞች ለመቋቋምና የጥፋት ዓላማቸውን ለማክሸፍ በከተማችን ከሚገኙ የፌደረሽኑ አባላት ጎን የምንቆም መሆናችንን እንገልጻለን።

ኢትዮጵያውያንና አሜሪካኖች ለፍትህና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ፤

ሎስ አንጅለስ